በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ
**Coordinating Committee of Exiled Members of Ethiopian Teachers Association**
የተሰጠ መግለጫ
ነሐሴ 11, 2004 ዓ/ም

# አገራችንን ከውድቀት ለመታደግ በሕብረት እንቁም፤ ለሥርዓት ለውጥ እንነሳ፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ባለው አልገዛም ባይነትና የነፃነት ተጋድሎ ግብፆችን፣ ድርቡሾችን፣ ቱርኮችንና ሌሎችንም በመጡበት መልሷቸዋል። በተለይ የኢጣሊያንን ፋሽስት የቅኝ አገዛዝ ሙከራ ከአንዴም ሁለት ጊዜ ድል መትቶ በማባረሩ የሁሉም ቅኝ ገዢዎችና ኃያላን ተብዬ አምባገነኖች ሸንፋት እንደሆነ አድርገው ዘመን እየቆጠሩ ተጠቃቅሰው ለማጥቃት ሲያደቡ ነው የቆዩት ከዚሁ ጋር ተያይዞ በመልከዓ ምድሯ ስትራቴጂአዊነት ሳቢያ ቢያንስ በተዘዋዋሪ በቁጥጥራቸው ሥር እንድትሆን ይሻሉ። እነርሱ በቀደዱት ቦይ የምትፈስ አገር እንድትሆንም አሻንጉሊት መንግሥት ተመስርቶ እንዲያገለግላቸው ይሠራሉ። ይህን እውን ለማድረግ እንደቀድሞው ባሕር አቋርጠውና ድንበር ጥሰው ጦርነት በማወጅ ሳይሆን በእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ስልት በመጠቀም ነው።

በዚህ ስልት ሲንቀሳቀሱም በሕዝብ መሀካል ያለውን የአስተዳደር ጉድለት፣ የሥልጣን ወይም የሀብት ክፍፍል መዛበት፣ባጠቃላይ የዲሞክራሲያዊ አካሄድ የተጎደሉበትን ክፍተት በመጠቀም ነው።ለዚህም ልዩልዩ ተቋሞችን በማቋቋም በዕርደታ ድርጅቶችና በሃይማኖት ስብከትም ሳይቀር ሰርገው ገብተው መረባቸውን ይዘረጋሉ። ሻዕቢያ፣ ወያኔና የመሳሰሉትን ፀረ-አንድነት ፣ፀረ-ዕድገት ፣ፀረ-ሕዝብና ፀረ-ኢትዮጵያዊነት አገር በቀል ጠላቶችን ያስታውሷል።እነዚህንና ሌሎችንም የገንዘብ የማቴሪያል፣ የሞራልና የፖለቲካ ድጋፍ አድርገው የ1983 ዓ፡ም ክስተት ጥሩ አጋጣሚ ፈጥሮላቸው ተረባረቡብን።የአገራችንን ሉዓላዊነት እንዲያደክሙና የራሳቸውን ፍላጎት አስፈጻሚ እንዲሆኑ ቡራኬ በለንደን ኮንፍረንስ ሰጥተው በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ በሃይል እንዲቀመጡ ተደረገ። የአገር ሉዓላዊነት፣ የሕዝብ ወሳኝነት፣ ታሪክ፣ ባሕል፣ ዕምነት፣ባጠቃላይ ሕዝባዊ እሴቶቻችን አደጋ ላይ ወደቁ።

ይህን አደጋ ለመቀልበስ ወሳኙ መፍትሔ ሥርዓቱን ከነሰንኮፉ ማስወገድ ብቻ ነው።ለዚህ ደግሞ የጋራ ትግል ማካሄድና ለሚከፈል መስዋዕትነት ሁሉ ተዘጋጅቶ በጽናት መቆምንም ይጠይቃል። እስካሁን በታየው ተመክሮ በሙያ ማህበራት፣በሠራተኞች፣ በፖለቲካ ድርጅቶች፣ በሃይማኖት ተቋሞችና በሌላውም የህብረተሰብ ክፍሎች ባንድነት የመቆም ጉዳይ በጥያቄ ዉስጥ ገብቷል።ለጥቃት ያጋለጠንም የወያኔ/ኢህአድግ ጥንካሬ ሳይሆን የአንድነት መንፈስ መላላት ነው። የአንድነታችን መዳከም ለዘረኛውና ለጠባቡ ወያኔ ቡድን ሥልጣን ይዞ እንዲቆይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል።ይባስ ብሎ የሚታየው ተግባራዊ እንቅስቃሴው የሥልጣን ዕድሜ በማራዘም የሚቆም ሳይሆን አገርን የማፍረስ ተልዕኮና ተግባሩን መቀጠሉ ነው ።ይህ የኢትዮጵያውያን ዋነኛው ስጋት ነው።ዳር ድንበራችን ተደፍሯል፣አገር ተቆርሷል፣ቅዱሳን የሃይማኖት ቦታዎች እንዲረክሱ ተደርጓል፣ ለም መሬታችን ከመሐል እስከ ዳር ለበዕድ ከበርቴዎች ወያኔ እየቸረቸረ ነው። ምርቱን እያየን ባሕር ተሻግሮ የሌሎች አገሮችን ዜጎች መዕድ ሲያትረፈርፍ የአገራችን ዜጎች ግን በፈረቃ እንኳን የሚመገብ ቤተሰብ ላይኖርና በርሃብ የሚረግፉ ወገኖቻችንን የምናይበት ጊዜ ላይ ደርሰናል።

በዚህ ሁሉ ችግር ተተብትበን፤ባልተቀናጀ መልኩም ቢሆን ሕዝባዊ አመጾች በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች እየተቀጣጠሉ ናቸው።እነዚህን በየቦታዉ የሚጨሱ ግለቶች ቋያ እሳት ሆነው ግፈኛውን ሥርዓት ዶጋ አመድ እንዲያደርጉ ማቀናጀት፣ ማስተባበርና መምራት ወቅታዊና ወሳኝም ነው።ማለፍ የማይገባቸው ጥሩ አጋጣሚዎች አምልጠዋል።ይህን በሚመመለከት በሰደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ "ስንት ዘንድሮ ያልፍብናል" በሚል ርዕስ በመገለጫው አመላክቷል። አሁን ያለውም ጥሩ ሁኔታ እንዳያመልጥ ተግቶ መስራት ከሁሉም ኢትዮጵያዊ የሚጠበቅ የዜግነት ግዴታ ነው። ይህ ካልሆነ ግን እንደላፈው ጊዜ ሁሉ ለወያኔ/ኢህአድግ የከፋፍለህ ግዛ ዘይቤው የልብልብ ሰጥቶት በዕብሪቱ አንዲቀጥል መንገድ ይከፍታል።

እላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በከፋፍለህ ግዛ የጎሳ ፖለቲካ ስልት የተካነው ወያኔ ያደረሰውአገር የማፍረስ እኩይ ተግባር፣ አፈናና፣የጭቆና አገዛዝ በአጠቃላይ የፖለቲካ፤የኢኮኖሚውና የማሕበራዊ ቀውሱ ሕዝቡን ለአመጽ ማነሳሰቱ ጥሩ አጋጣሚ፤ የሚደገፍና፣የሚበረታታ በመሆኑ ቅን ልቦና ላለው ዜጋ ሁሉ ተስፋ ሰጪ ነው።ሁኔታው የሚያሳየው ሕዝቡ በራሱ አነሳሽነት አመጹን

እያካሄደ እንደሆነ ነው።የሕዝቡ ተነሳሽነትና ተግባራዊ እንቅስቃሴ የሚደነቅ የመሆኑን ያህል በኢትዮጵያ አንድነትና በሕዝብ የበላይነት እናምናለን የሚሉ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ጠንክረው ወጥተው በአገር ውስጥ ሆነው በግልጽም በሕቡዕም ሕዝባዊ ትግሉን የማስተባበርና የመምራት ሚናቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል።የወያኔ ሥርዓት መወገድ እንዳለበት ከታመነበት ትግሉን ማን ይምራው የሚል ጥያቄ መነሳቱ ስለማይቀር ለዚህ ስነልቦናዊ ዝግጅትና ምላሽ መስጠት ያስፈልጋል።ባጠቃላይ ሲታይ በአገር ላይ ያንዣበበው አደጋ መቀልበስ እንዳለበት የኢትዮጵያውያን ፍላጎት ነው።ለዚህ ዓላማ ግብ መድረስ እያንዳንዱ የበኩሉን አስዋጾኦ ማድረግ የሚገባው መሆኑ አያጠያይቅም። ግዴታም ነው።አገር እየጠፋ እንዴት ዝም ተብሎ ይታያል?

ከዚህ አንፃር ሁሉም ያገባናል የሚሉ በኢትዮጵያ አንድነት የሚያምኑ የፖለቲካ ድርጅቶች፤የሲቪል ማሕበራት ሁሉ ትግላቸውን በማስተባበር የወያኔን የጎሳ ሥርአት በመገርሰስና ዲሞክራሲያዊ ሕዝባዊ ሥርአትን ለመገንባት አምርረው መታገል ይኖርባቸዋል ለዚም በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ የበኩሉን ድርሻ ለመወጣት ዝግጁ ነው። አገራችንን ከውድቀት ለመታደግ መፍትሔውና መቋጫው በሕብረት መቆምና ለሥር ነቀል ለውጥ መነሳት ነው። የኢትዮጵያ መምህራንና ማህበራችው ኢማማ ለወያኔ በየወቅቱ ባቀረቧቸው የመብትና የዲሞክራሲያዊ ጥያቄዎች ምላሽ ያለማግኘት እንዳሉ ሆኖ ከዚህ አጅግ በላቀ ደረጃ የአገርና የሕዝብ ሕልዉና ላይ የሚያተኩሩበትና የሚታገሉበት ፈታኝ ምዕራፍ ላይ መድረሳቸውን ተገንዝበዋል። ለዚህም ነዉ የዚህ መግለጫ ይዘት ባመዘኙ የአገሪቱን ጉዳይ ቅድሚያ የሰጠው። ሕዝባዊ ሥርዓትና መልካም አስተዳደር በሌሉበት የሥራ ዋስትና ፤የሙያ ክብር ፤ የመደራጀት ነፃነት፣የአካዳሚ ነፃነት---ሊከበሩ እንደማይችሉ ገሃድ ነዉ። በመጨረሻም በሰደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ ቀጥሎ ላሉት አካላት መልዕክቱንና ጥሪውን ያስተላልፋል፡-

- ወያኔ ካባረራቸው መምህራን መካከል ከአማራዉ ክልል ስምንቱም ወደ ሥራቸዉ መመለሳቸዉ ተረጋግጧል። ከአዲስ አበባ ክሥራቸዉ የተበረሩት አምስቱም መምህራን ወደ ሥራቸዉ ያልተመለሱ ስለሆነ በ2005 ዓ.ም ትምህርት ቤቶች ሲከፈቱ የመምህራንና የተማሪዎች ጥያቄ እነዚህ መምህራን ወደ ሥራቸዉ አንዲመለሱ እንዲጠይቁ፣ እንዲሁም ሌላዉ የህብረተሰብ ክፍል ለተባረሩት መምህራን ሁለንታናዊ ድጋፍ እንዲያደርጉ፣

- ተማሪዎች ከመምህራን ጋር በመሆን የመደራጀት ነፃነት (የተማሪዎች ም/ቤት እንዲቋቋም)፣የአካዳሚ ነፃነት፣ ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች የሚያካሄዱትን የመብት ትግል ማገዝ፣ ለሥርዓት ለዉጥ መታገል፣ ት/ቤቶች የካድሬመፈልፈያና የአፋና ተቋማት እንዳይሆኑ መከላከል፣ ጥራት ያለዉ ትምህርት እንዲሠራጭና ውጤታማ እንዲሆን እንዲታገሉ፣
- ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች፤ ሠራተኛው፣ ገበሬው፣ ታክሲ ነጂው፣ሴቶች፣ ወጣቶች፣ --- ይህን ዘረኛ ሥርዓት ለማስወገድ ትብብር እንዲያደርጉ፣ እንዲነሱ
- የተለያዩ የዕምነት ተቋማት የኦርቶዶክስና የእስልምና ዕምነት ተከታይ ምዕመናን እያደረጉ ያሉትን የመብት ጥያቄዎች ትግል ውጤት እንዲያመጣ ሕብረት በመፍጠር እንዲታገሉና ለድል እንዲበቁ፣ሌሎችም የተለየዩ ዕምነት ተከታዮች ይህን ትግል እንዲያግዙ፣እንዲነሱ
- ወያኔ ከኢማማ የውስጥ ጉዳይ ፣ከኢትዮጵያ ሙስሊሞች የመብት ጥያቄ ጉዳይ፣በኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ ዕምነት ተቋማት ላይ የሚያካሄደውን ሕገወጥ ጣልቃ ገብነት እንዲያቆም፣
- ዳር ድንበር ለመጠበቅ የተቋቋመው መደበኛ ሠራዊት በሕዝብ ላይ የሚፈጽመውን በደል እንዲያቆምና ከሕዝብ ጎን እንዲ ሰላፍ፣ የሰላም ዘብ መሆን የሚገባው ፖሊስ በሕዝብ ላይ የሚያደርሰውን የመብት ረገጣና ሠላም የማደፍረስ ተግባሩን አቁሞ ከሕዝብ ጎን እንዲሰለፍ፣የአገር ደህንነት ክፍል የሥለላ ተቋም በዜጎች ላይ የሚፈጽመውን አፋና፣መሰወር፣ ማሰቃየትና ግድያ በማቆም ከሕዝብ ጎን እንዲሰለፍ መልዕክታችንና ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

መተባበር የወቅቱ ጥያቄ ነው!!
መምህራን የሙያና የዜግነት ግዳጃቸውን በትግላቸው ይወጣሉ!!
ያለመስዋዕትነት ድልና ነፃነት አይረጋገጡም!!
ለበለጠ መረጃ eta1941@yahoo.com በመጻፍ ሊያገኙን ይችላሉ